ኦረንጌዴ የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤቶች ህብረት ሰራ ማህበር
በማህበሩ እና በቤትባለቤቶች /ተወካዮች/መካከልየሚደረግየእድሳትውል

የቤት እድለኛ ሙሉ ስም: _____**የተወካይ ሙሉ ስም** _____

የሕንፃ ቁጥር: _____**የወለል ቁጥር:** _____**የቤት ቁጥር:** _____**ስልክ ቁጥር:** _____

ማንኛውም የቤት እድለኛ ቤቱን ሲረከብ ያልተጠናቀቁ ስራዎችን የመጨረስ፤የቤቱ የውስጥ አካል የሆነውን ማደስእና ማስዋብ እንደሚችል እሙን ነው::ነገር ግን በመጨረስ፣ በማደስ እና በማስዋብ ስራ ላይ በሌላ አካል ንብረት ላይ ወይም በሕንፃው ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ማድረስ አይኖርበትም::በመሆኑም ማንኛውም የቤት እድለኛ ቤቱን በሚጨርስበት፣ በሚያድስበት ወይም በሚያስውብበት ወቅት ሊያደርጋቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጥንቃቄዎች የሚከተሉት ናቸው::

1. በማንኛውም ጊዜ እድሳት ሲከናወን ለዚሁ ተብሎ የተዘጋጀ ይህንን ቅፅ በመሙላት ለኮሚቴው ማሳወቅ እና ማፀደቅ ይኖርበታል::ከቅፁ ጋር በአባሪነት የሚሰሩ ስራዎች ዝርዝር በቅደም ተከተል ተቀምጧል።ሁሉም ስራዎች በዚህ ዝርዝር መሠረት ቅደም ተከተላቸውን እንደጠበቁ መሠራት አለባቸው።የስራ ሂደት ለውጥ የሚያስፈልገው ከሆነ በጎረቤቶችና በቴክኒክ ኮሚቴው ከታመነበት ብቻ ሊቀየር ይችላል።
2. ማንኛውም የእድሳት ስራ ከመጀመሩ በፊት የሚሰሩት ባለሞያዎች ስም፣ሙያ እና አድራሻ ለኮሚቴው ማሳወቅ እና ማስመዝገብ ያስፈልጋል።በተጨማሪም የሚገቡት ግብአቶች እና መሳሪያዎች መመዝገብ አለባቸው። ስራዎች መጠናቀቃቸዉን የሚገልፅ ቅፅ በመሙላት ተርፎ የሚወጣዉን ግብዓት ማሳወቅ ይኖርበታል::
3. ስርቆትን ለመቆጣጠር ይረዳ ዘንድ ማንኛዉም ቅጥር ሰራተኛ (ባለሞያም ሆነ ቀን ሰራተኛ) በማህበሩ ለቤት ባለቤት የተሰጠ መታወቂያ ኮፒ ሊኖረዉ ይገባል::ተቀጣሪዉ ስራ ሲጀምር ለተረኛ የህንፃዉ ጥበቃ አንድ የመታወቂያ ኮፒ መስጠት እና ከዋናዉ ጋር እንዲገናዘብ ማድረግ ይኖርበታል::ወጪውም በባለቤቱ የሚሸፈን ይሆናል።
4. በቅጥር ሰራተኝነት ተቀጥሮ በቆይታዉ ወቅት ስርቆት ከፈፀመ ወይም ሌላ ያልተገባ ባህሪ ካሳየ ቀጣሪዉ በ24 ሰዓት ውስጥ ለኮሚቴዉ ማሳወቅ አለበት::በተመሳሳይ የሞያ ችግር ካለበት ቀጣሪዉ ለኮሚቴዉ ማሳወቅ አለበት::
5. በአግባቡ እና በጥንቃቄ ያልተሰራ ስራ ወደፊት የተሰራዉን ስራ ሊያስፈርስ እና በሌሎች ቤቶች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል በሚታደስበት ወቅት አስፈላጊውን ጥንቃቄ እና መከላከያ ነገሮችን (water proof) መጠቀም ግድ ይላል::በመሆኑም ማንኛዉም የሴራሚክ ወለል ንጣፍ በሚነጠፍበት ጊዜ የዉሃ ስርገት መከላከያ እንዲጠቀሙ ይመከራል::ነገር ግን የመታጠቢያ ቤት / ቤቶች እና የማብሰያ ቤት የሴራሚክ ወለል ንጣፍ በሚቀየርበት ወቅት የዉሃ ስርገት መከላከያ የግድ መጠቀም ያስፈልጋል::በመሆኑም የዉሃ ስርገት መከላከያ በሚቀባበት ጊዜ ለሚመለከተዉ አካል በማሳየት እና ቀጣዩን የሴራሚክ ንጣፍ ስራ ለመቀጠል የፅሁፍ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል::ይህ ሳይደረግ የተከናወነ የመታጠቢያ ቤት /ቤቶች እና የማብሰያ ቤት የሴራሚክ ወለል ንጣፍ ስራ ማህበሩ አስፈርሶ በድጋሚ በአግባቡ እንዲሰራ ያደርጋል :: በተጨማሪም ለተሰራዉ ጥፋት ቅጣት ያስከፍላል::
6. በር ሳይቆለፍ ወይም ተቀጣሪ ሰራተኛ እያለ ለጠፋ እቃ ማህበሩም ሆነ የማህበሩ የጥበቃ ሰራተኞች ተጠያቂ አይሆኑም::የውጭ በር ቁልፍ አንድ ኮፒ ጥበቃ ጋር መቀመጥ አለበት።
7. ስራዎች በሚከናወኑበት ወቅት የሚወገድ ማንኛዉም ተረፈ ምርት መወገድ ያለበት በማህበሩ በተፈቀደ ቦታ ብቻ መሆን አለበት::በሊፍት ከፍት ቦታዎች ላይ ፍራሽ ማሰውግድ በጥብቅ የተከለከለ እና ተጠያቂ የሚያደርግ ይሆናል::
8. ማደስ ወይም ማሳመር የሚቻለዉ የግል ቤት የዉስጥ አካል ብቻ ይሆናል::የጋራ መጠቀሚያን ወይም የሕንፃ የዉጪ አካል ማደስ ወይም ማሳመር በፍፁም የተከለከለ ነዉ::
9. ከላይ በተራ ቁጥር 1 እስከ 8 የተረዘረዘሩትን ነጥቦች ከግምት ዉስጥ በማስገባት የቤት እድለኞች ቤታቸዉን በጥንቃቄ እና ኃላፊነት በተሞላበት፣የሌላሰውን ቤት ወይም የሕንፃዉ አካል ላይ ጉዳት በማያደርስ መልኩ ስራዎችን መስራት ይኖርባቸዋል::ይሁንና በቸልተኝነትም ሆነ በስህተት ይህንን መመሪያ ያላከበረ ለሚደርሰዉ ማንኛዉም ጥፋት ጉዳት የደረሰበትን ነገር በአንድሳምንት ዉስጥ ወደነበረበት መልሶ በማህበሩ የዉስጠ ደንብ መሰረት የተጣለዉን ቅጣት የሚከፍል ይሆናል::ማህበሩም ይህንን ለማስፈፀም የክትትል ኮሚቴ አቋቁሞ ጥብቅ ክትትል ያደርጋል::

ኦረንጌዴ የጋራ ህንጻ ቤት ባለቤቶች ህብረት ሰራ ማህበር
በማህበሩ እና በቤትባለቤቶች /ተወካዮች/መካከልየሚደረግየእድሳትውል

1O. ከዚህ የእድሳት ውል ጋር አብሮ በአባሪነት የተያያዘውን የእድሳ ትመመሪያ እና የእድሳት ስራዎች ዝርዝር በቅደም ተከተሉ መሠረት አለማከበር እና አለመከተል የእድሳት ውልን አስከማቋረጥ ድረስ ያስቀጣል።

11. በእድሳት ወቅት ቀጥተኛ ክትትል ማድርግ በየህንጻው የተዋቀረው ንዑስ ኮሚቴ ሀላፊነት ይሆናል።

ዉል ተቀባይ

እኔ አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት _____ ከላይ በተቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ቤቴን ለመጨረስ / ለማደስ ተስማምቼ ዉል ገብቻለሁ።በመሆኑም በእኔ ምክንያት በሌላ ሰው ቤት ላይ ለሚደርስ ማንኛዉም ጥፋት ወደቦታዉ ለመመለስ እና የተወሰነዉን የቅጣት መጠን ለመክፈል ተስማምቻለሁ።

ስም_____**ፊርማ** _____**ቀን**_____

የማህበሩ ተወካይ ስም..... **ፊርማ**.....**ቀን**.....